# የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በሽያጭ ወደ ግል ይዞታ ለማዛወር የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

**የጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር- 001/2019-2020**

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ቀጥሎ የተመለከተው እርሻ ሙሉ በሙሉ ባለቤት ነው፡፡
2. የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ በመቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 445/2011 በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሠረት ከዚህ ቀጥሎ የተጠቀሰውን ድርጅት ለመምራትና ለማስፋፋት ፈቃደኛ ለሆኑና አቅም ላላቸው ባለሃብቶች **በሽያጭ የጨረታ. 001/2019-2020** ለማስተላለፍ ይፈልጋል፡
3. **ለሽያጭ የቀረበ ደርጅት፡**
   - አባያ እርሻ ……………………………………………………አባያ/ወላይታ ሶዶ
4. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና በጨረታ ሰነዱ ውስጥ በተጠቀሰው መሰረት ማቅረብ አለባቸው፡፡
5. ተጫራቾች በዚህ ጨረታ አፈጻጸም የተዘጋጁትን የጨረታ ሠነዶች ገርጂ በሚገኘው ውሃ ሥራ ዲዛይንና ቁጥጥር ድርጅት ህንጻ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 204 በመቅረብ ለእያንዳንዱ የጨረታ ሠነድ ተመላሽ የማይደረግ ብር 300.00 (ሦስት መቶ ብር) ወይም የዚህን ተመጣጣኝ የሆነ በአሜሪካን ዶላር በመክፈል ከሚያዚያ 30 ቀን 2012 ዓ.ም. ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሠዓት መውሰድ ይችላሉ፡፡
6. ተጫራቾች የጨረታ ፕሮፖዛላቸውን ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ፣ የተጫረቱበትን ድርጅት ስምና የጨረታ ቁጥሩን በመጥቀስ በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከቀኑ 9፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት አለባቸው፡፡
7. ጨረታው ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም.. ከቀኑ በ9፡15 ሰዓት በ2ኛ ፎቅ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
8. ተጫራቾች ፕሮፖዛል የሚያቀርቡበት ቀን እስከ ሰኔ 30 ቀን 2012 ዓ.ም ከቀኑ በ9፡00 ሲሆን ከዚህ ዘግይቶ የመጣ ፕሮፖዛል ተቀባይነት የለውም፡፡
9. ኤጀንሲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
10. ተጫራቾች የጨረታ ፕሮፖዛላቸወን የሚያቀርቡት በሚከተለው አድራሻ ይሆናል፡፡

**የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ**

**ስልክ፡-** 011 8 69 37 29/0118693781

**ፖ.ሣ.ቁ.** 11835

**ገርጂ በቀድሞው ኢምፔሪያል ሆቴል ፊት ለፊት ባለው ውሃ ሥራዎች ዲዛይንና**

**ቁጥጥር ድርጅት ህንጻ 2ኛ ፎቅ    ቢሮ ቁጥር 204**

**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

**በጨረታ ማስታወቂያ ቁጥር 001/2019-2020 መሠረት ለአባያ እርሻ የቀረበ የጨረታ ፕሮፖዛል በማለት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡**

**የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ**